Ayalew Bitane Law Office
09119113131

## የገቢዎች ሚኒስቴር

# የታክስ አስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ መመሪያ ቁጥር …/2016

ሚያዝያ 2016 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# የታክስ አስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ መመሪያ ቁጥር /2016

የታክስ ባለሥልጣኑ የቅጣት ይነሳልኝ ማመልከቻ ሲቀርብለት ወይም በራሱ ተነሳሽነት በታክስ ከፋይ ላይ የተጣለን አስተዳደራዊ ቅጣት በሙሉ ወይም በከፊል ሊያነሳ እንደሚችል በፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ የተደነገገ በመሆኑ፤

ታክስ ከፋዮች በልዩ ልዩ ምክንያቶች በህግ በተመለከተው መሠረት ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው ወይም መወጣት ባለመቻላቸው የሚጣልባቸው አስተዳደራዊ ቅጣት ታክሱን ለመክፈል ፍቃደኛ ቢሆኑም ቅጣቱ እስካልተቃለለ ድረስ የመክፈል አቅማቸው የሚዳከም በመሆኑ፤

አስተዳደራዊ ቅጣት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ማንሳት ታክስ ከፋዮች ውዝፍ ፍሬ ታክስ ሳይዘገይ ለመሰብሰብ የሚያስችል መሆኑ ስለታመነበት እና ቅጣቱ በሙሉ ወይም በከፊል መነሳት የአስተዳደራዊ ቅጣት አላማን በጠበቀ ሁኔታ እንዲፈጸም ለማድረግ የቅጣት ደረጃ ምደባዎችን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ቀድሞ ሥራ ላይ በነበረ የቅጣት አነሳስ መመሪያ ያልተሸፈኑ አስተዳደራዊ ቅጣቶች እንዲካተቱ ማድረግ፣ የቅጣት አነሳስ ሁኔታው ፍትሃዊ እንዲሆን ማድረግ እና ቅጣቱን ስለሚያነሳ የሥራ ክፍል በይበልጥ ግልጽ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በዚሁ መሠረት የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር በፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 115(4) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ **"የታክስ አስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ መመሪያ ቁጥር -------2016"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

ለዚህ መመሪያ አፈጻፀም የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር፡-

1) **"የታክስ ህግ"** ማለት በአዋጁ አንቀጽ 2(36) የተሰጠዉን ትርጉም ይይዛል፡፡

2) **"አስተዳደራዊ ቅጣት"** ማለት በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 2(24) ላይ የተቀመጠዉን ትርጉም የሚይዝ ሆኖ የወጪ መጋራት እና የጡረታ መዋጮ ግዴታን ባለመወጣት የሚጣል ቅጣትን አይጨምርም፡፡

3) **"የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል"** ማለት በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 55(1) በአዋጁ መሰረት ባለስልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተቋቋመ፣ በአስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ ላይ በተሰጠ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ሲቀርብ በማጣራት ለቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ የዉሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ የስራ ክፍል ነው፡፡

4) **"ሐራጅ/ጨረታ"** ማለት የታክስ ዕዳን ባለመክፈል በታክስ ባለስልጣኑ የተያዘን ንብረት በግልጽ ጨረታ ሥነ-ሥርዓት የመሸጥ ሂደት ነዉ፡፡

5) **"ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት"** ማለት ታክስ ከፋዩ በራሱ ሊያስወግደዉ የማይችል የተፈጥሮ ወይም ሰዉ ሰራሽ አደጋ ወይም ጽኑ ህመም ወይም ታክስ የመክፈልና ሌሎች ግዴታዎችን እንዳይወጣ የሚያደርግ ተጨባጭ እና የተረጋገጠ ምክንያት ነዉ፡፡

6) **"ጽኑ ህመም"** ማለት ታክስ ከፋይ የዉሳኔ ማስታወቂያ ከደረሰዉ ወይም አስታውቆ መክፈል ባለበት ጊዜ ዉሰጥ ተንቀሳቅሶ መስራት የማያስችል ህመም ላይ ስለመሆኑ በታወቀ የህክምና ተቋም በህክምና ማስረጃ የተረጋገጠ ሆኖ በጊዜው የንግድ ስራ እንቅስቃሴዉን የሚመራለት የታክስ እንደራሴ የሌለው ሲሆን ነው፡፡

7) **"የቅጣት ደረጃ ምደባ"** ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት በከፊል የሚነሳ አስተዳደራዊ ቅጣት ለመወሰን ሲባል በታክስ ህጎች የተዘረዘሩትን አስተዳደራዊ ቅጣቶች ዝቅተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ ደረጃ በማለት የተደለደለበት የቅጣት ምደባ ደረጃ ነዉ፡፡

8) **"የታክስ ባለስልጣን"** ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ሲሆን፣ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮዎችን ይጨምራል፡፡

9) **"አዋጅ"** ማለት የፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ነዉ፡፡

10) በዚህ መመሪያ ትርጉም ያልተሰጣቸዉ ቃላትና ሀረጎች እንደሁኔታዉ በታክስ አስተዳደር አዋጅና በታክስ ህጎች ዉስጥ የተሰጣቸዉን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

3. **የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በታክስ አስተዳደር አዋጅ፣ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ እና በቴምብር ቀረጥ አዋጅ መሰረት በተጣለ የታክስ አስተዳደራዊ ቅጣት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## አስተዳደራዊ ቅጣት የሚነሳበት ሁኔታ እና መጣኔ

4. **አስተዳደራዊ ቅጣት የሚነሳበት እና የማይነሳበት ሁኔታ**

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12 እና 13 ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆኖ በታክስ ህግ የተጣሉ አስተዳደራዊ ቅጣቶች ከዚህ በታች በተደነገገዉ መሰረት በከፊል ወይም በሙሉ ሊነሱ ይችላሉ፡፡
2) በአዋጁ አንቀጽ 108 (የታክስ ደረሰኝ አለመስጠት) እና በቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 110/1990 አንቀጽ 10(3) መሠረት የተጣለ ቅጣት የሚነሳ አይሆንም፡፡

5. **የአስተዳደራዊ ቅጣቶች ደረጃ ምደባ**

በታክስ አስተዳደር አዋጅ፣ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ እና በቴምብር ቀረጥ አዋጅ መሰረት የተጣለ አስተዳደራዊ ቅጣት የአንድን ድርጊት መፈፀም ወይም አለመፈፀም በታክስ አስተዳደርና በታክስ አሰባሰቡ ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ወይም ተጽዕኖ መሰረት በማድረግ ቅጣቶች በዝቅተኛ፣መካከለኛና ከፍተኛ ደረጃ ተመድቧል፡-

1) የአዋጁ አንቀጽ 101፣ 103፣ 109፣ እና 112 በዝቅተኛ የቅጣት ደረጃ፤

2) የአዋጁ አንቀጽ 104፣105፣ 106፣ 107 (ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3)፣ 111 እና 114 (ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 6)፣ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 አንቀጽ 38(1-3) የተጣለ ቅጣት በመካከለኛ የቅጣት ደረጃ፤

3) የአዋጁ አንቀጽ 102፣ 107(4)፤ 110፤ 113 እና 114(7) ቅጣት በከፍተኛ የቅጣት ደረጃ

ተመድበዋል፡፡

## 6. አስተዳደራዊ ቅጣት በከፊል የሚነሳበት መስፈርትና ምጣኔ

ከላይ በአንቀጽ 5 በተደነገጉት የቅጣት ደረጃዎችና የታክስ ዕዳዉ የተከፈለበትን ጊዜ እና ሁኔታ መሰረት በማድረግ ቀጥሎ በተገለፀዉ መሰፈርትና ምጣኔ መሰረት አስተዳደራዊ ቅጣቶች በከፊል ሊነሱ ይችላሉ፤

| ተ.ቁ | ፍሬ ታክስ፣ ወለድ እና የማይነሳውን ቅጣት የተከፈለበት ጊዜ | የሚነሳው ቅጣት ምጣኔ በቅጣት ደረጃ ምደባ መስረት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | በዝቅተኛ ደረጃ የሚመደብ ቅጣት | በመካከለኛ ደረጃ የሚመደብ ቅጣት | በከፍተኛ ደረጃ የሚመደብ ቅጣት |
| 1 | ታክስ ከፋዩ የታክስ ዉሳኔ ማስታወቂያ ወይም በቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል ወይም በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም በፍ/ቤት ዉሳኔ መሠረት የተሰጠ የታክስ ማስታወቂያ በደረሰዉ በ30 ቀን ውስጥ ቀርቦ፡- | | | |
| 1.1 | በአንድ ጊዜ አጠቃሎ ከከፈለ | 90 | 80 | 70 |
| 1.2 | ባለስልጣኑ በሚሰጠዉ እስከ 6 ወራት በሚደርስ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ከከፈለ | 80 | 70 | 60 |
| 1.3 | ባለስልጣኑ በሚሰጠዉ ከ6 ወራት በላይ በሆነ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ከከፈለ | 70 | 60 | 50 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 2 | ታክስ ከፋዩ የታክስ ዉሳኔ ማስታወቂያ ወይም በቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል ወይም በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም በፍ/ቤት ዉሳኔ መሠረት የተሰጠ የታክስ ማስታወቂያ በደረሰዉ ከ31 እስከ 60 ቀን ባለው ጊዜ ቀርቦ፡- | | | |
| 2.1 | በአንድ ጊዜ አጠቃሎ ከከፈለ | 80 | 70 | 60 |
| 2.2 | ባለስልጣኑ በሚሰጠዉ እስከ 6 ወራት በሚደርስ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ከከፈለ | 70 | 60 | 50 |
| 2.3 | ባለስልጣኑ በሚሰጠዉ ከ6 ወራት በላይ በሆነ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ከከፈለ፣ | 60 | 50 | 40 |
| 3 | ታክስ ከፋዩ የታክስ ዉሳኔ ማስታወቂያ ወይም በቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል ወይም በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም በፍ/ቤት ዉሳኔ መሠረት የተሰጠ የታክስ ማስታወቂያ ደርሶት የሚፈለግበትን ታክስ ሳይከፍል 60 ቀን ያለፈው ሆኖ ቀርቦ፡- | | | |
| 3.1 | በአንድ ጊዜ አጠቃሎ ከከፈለ | 70 | 60 | 50 |
| 3.2 | ባለስልጣኑ በሚሰጠዉ እስከ 6 ወራት በሚደርስ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ከከፈለ | 60 | 50 | 40 |
| 3.3 | ባለስልጣኑ በሚሰጠዉ ከ6 ወራት በላይ በሆነ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ከከፈለ | 50 | 40 | 30 |
| 4 | ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ታክስ ባለመክፈሉ ሀብቱ ከተያዘ በኋላ ሀራጅ ወይም የጨረታ ማስታወቂያ ሳይወጣ ቀርቦ ፡- | | | |
| 4.1 | በአንድ ጊዜ አጠቃሎ ከከፈለ | 60 | 50 | 40 |
| 4.2 | ባለስልጣኑ በሚሰጠዉ እስከ 6 ወራት በሚደርስ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ከከፈለ | 50 | 40 | 30 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 4.3 | ባለስልጣኑ በሚሰጠዉ ከ6 ወራት በላይ በሆነ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ከከፈለ | 40 | 30 | 20 |
| 5 | ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ታክስ ባለመክፈሉ በሀብቱ ላይ የሀራጅ ወይም የጨረታ ማስታወቂያ ከወጣ በኋላ ቀርቦ፡- | | | |
| 5.1 | በአንድ ጊዜ አጠቃሎ ከከፈለ | 50 | 40 | 30 |
| 5.2 | ባለስልጣኑ በሚሰጠዉ እስከ 6 ወራት በሚደርስ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ከከፈለ | 40 | 30 | 20 |
| 5.3 | ባለስልጣኑ በሚሰጠዉ ከ6 ወራት በላይ በሆነ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ከከፈለ | 30 | 20 | 10 |

7. <u>አስተዳደራዊ ቅጣት ሙሉ በሙሉ የሚነሳበት ሁኔታ፡-</u>

1) ከዚህ ቀጥሎ በተገለጹ ምክንያቶች በታክስ ከፋዩ የተጣለ አስተዳደራዊ ቅጣት ሙሉ በሙሉ ሊነሳ ይችላል፡-

ሀ) ታክስ ከፋዩ የታክስ ግዴታውን በመክፈያ ጊዜው እንዳይከፍል የሚያደርግ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ያጋጠመው ከሆነ፤

ለ) የድርጅቱ የንግድ ሥራ ሊቀጥል የማይችል እና የከሠረ (bankrupt) መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ፤

ሐ) ባለሥልጣኑ የታክስ ከፋዩን ሒሳብ ከመመርመሩ በፊት ታክስ ከፋዩ ስህተቱን በራሱ ተነሳሽነት ያረመ እንደሆነና በተሻሻለው የታክስ ስሌት መሠረት ፍሬ ታክስና ወለድ ከከፈለ፤

መ) ከንብረቱ 20 በመቶ እና ከዚያ በላይ በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ ምክንያት የወደመበት መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ከሚመለከተው የመንግስት ተቋም ያቀረበ ከሆነ፤

ሠ) ከራሱ ገቢ ላይ ግብር ቀንሶ የሚያስቀር ተቀጣሪ በሥራ ላይ እያለም ሆነ የሥራ

ውሉ ሲቋረጥ፤

ረ) ለቅጣቱ ምክንያት የሆነው ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በፈጠረው የአሠራር ስህተት መሆኑ ከተረጋገጠ፡፡

ሰ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 የተገለጸው ቢኖርም ከወርሃዊ ማሳወቂያ ጋር በተያያዘ በመክፈያ ጊዜው ግብር ከፋዩ ባንክ ገቢ በሚያደርግበት ጊዜ በወቅቱ ቀርቦ ደረሰኝ ባለማስቀረጥ ምክንያት በሲስተም የሚሰላው ቅጣት፤

2) ታክስ ከፋዩ የታክስ ዉሳኔ ማስታወቂያ ወይም በቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል ወይም በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም በፍ/ቤት ዉሳኔ መሠረት የተሰጠ የታክስ ማስታወቂያ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ፍሬ ታክሱን፣ ወለዱን፣ እና በከፍተኛ እና በመካከለኛ ደረጃ ለተመደበ ቅጣት በአንቀጽ 6 በተቀመጠው ሠንጠረዥ ተ.ቁ 1.1 መሠረት ከከፈለ፣ በታክስ ውሳኔው ውስጥ የሚገኝ በዝቅተኛ የቅጣት ደረጃ የተመደበ አስተዳደራዊ ቅጣት ሙሉ በሙሉ ሊነሳ ይችላል፡፡

## 8. የቅጣት ይነሳልኝ ጥያቄ አቀራረብ

1) አስተዳደራዊ ቅጣት የተወሰነበት ሰው ቅጣቱ እንዲነሳለት ምክንያቱን በመግለጽ ለባለስልጣኑ ቅ/ጽ/ቤት ለታክስ ዕዳ አስተዳደር የሥራ ሂደት ወይም ለታክስ ኦፕሬሽን የሥራ ሂደት መሪ ወይም ለታክስ ማዕከል አስተባባሪ በጽሑፍ ማመልከት አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው ቢኖርም የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት የገቡ ፍሬ ታክሱን፣ ወለዱንና የማይነሳውን ቅጣት ከፍለው ከጨረሱ ማመልከቻ ማቅረብ ሳያስፈልግ ቅጣቱ የሚነሳ ይሆናል፡፡

## 9. ቅጣትን የማንሳት ሥልጣን

1) የታክስ ዕዳ አስተዳደር የሥራ ሂደት፣ የታክስ ኦፕሬሽን የሥራ ሂደት መሪ፤ የታክስ ማዕከል አስተባባሪ፤ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 እና 7 መሠረት ቅጣት ያነሳሉ፡፡

2) አስተዳደራዊ ቅጣቱ ስለመነሳቱ ለዚህ አላማ በተዘጋጀ ቅጽ ተሞልቶ በሥራ ሂደቱ ከተረጋገጠና ከጸደቀ በኋላ የሚከፈለው ታክስ፣ ወለድና የማይነሳው የቅጣት መጠን ተከፍሎ ቀሪው ቅጣት ዕዳውን በሚከታተለው የዕዳ ክትትልና አሰባሰብ ባለሙያ ከሲስተም(ሲግታስ) ላይ ተገቢው መግለጫ ሰፍሮ እንዲሰረዝ ይደረጋል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የታክስ ዕዳ አስተዳደር የሥራ ሂደት ወይም የታክስ ኦፕሬሽን የሥራ ሂደት መሪ ወይም የታክስ ማዕከል አስተባባሪ በሚወስነው የቅጣት አነሳስ ላይ በታክስ ከፋይ የሚቀርብ ቅሬታ በቅ/ጽ/ቤቱ የተቋቋመው የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ሥራ ክፍል ቅሬታውን በመቀበል ምርምሮ ለቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ የውሳኔ ሃሳብ በማቅረብ ያስወስናል፡፡በውሳኔው መሠረት ተፈጻሚ ይደረጋል፡፡

## 10. <u>አስተዳደራዊ ቅጣትን በልዩ ሁኔታ ስለማንሳት</u>

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4(2)፣ 6 እና 7 ላይ የተመለከተው ቢኖርም በኢኮኖሚያዊ፣ አስተዳደራዊ ወይም ማህበራዊ ምክንያቶች የታክስ ባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ ወይም የሚወክለው ኃላፊ በታክስ ከፋዩ ጥያቄ መሠረት ወይም በታክስ ባለሥልጣኑ የራስ ተነሳሽነት መሠረት የተጣለን አስተዳደራዊ ቅጣት በልዩ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሊያነሳ ይችላል፡፡

2) በልዩ ሁኔታ የሚታይ የቅጣት ይነሳልኝ ጥያቄ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤት መቅረብ ያለበት ሲሆን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ጥያቄውን ከታክስ ከፋዩ የሚፈለግ ጠቅላላ የታክስ ዕዳ መጠን፣ የታክስ አይነት፣ የታክስ ዕዳው ያለበት ሁኔታ፣ የታክስ ከፋዩ የታክስ አከፋፈል ታሪክ፣ በልዩ ሁኔታ ቅጣት እንዲነሳ የተጠየቀበትን ተጨባጭ ምክንያትና ማስረጃ፣ እንዲሁም በጉዳዩ ላይ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ዝርዝር የውሳኔ ሃሳብ በሥራ አስኪያጁ ተፈርሞ በዋና መሥሪያ ቤት ላለው የታክስ ዕዳ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት መላክ አለበት፡፡

3) የታክስ ዕዳ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ እንዲሁም የግብር ከፋዩን ጥያቄ እና ስለጉዳዩ የቀረበውን ማስረጃ መርምሮ ለታክስ ባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ ወይም ለሚወክለው ኃላፊ ዝርዝር የውሳኔ ሀሳብ በማቅረብ አስተዳደራዊ ቅጣቱ በልዩ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲነሳ ለውሳኔ ያቀርባል፡፡

4) ለታክስ ባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ ወይም ለሚወክለው ኃላፊ ቀርቦ በሚወሰነው ውሳኔ መሠረት እንዲፈጸም በታክስ ዕዳ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በኩል ለቅ/ጽ/ቤቱ የሚላክ

ሆኖ የሚነሳው አስተዳደራዊ ቅጣት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9(2) መሠረት ተፈጻሚ የሚደረግ ይሆናል፡፡

## 11. ለቅጣት አነሳስ የክፍያ ጊዜ ስምምነት ስለሚፈጸምበት ሥርዓት

1) በክፍያ ጊዜ ስምምነት መመሪያ መሠረት የታክስ ዕዳውን በተራዘመ ጊዜ ለማስከፈል ከግብር ከፋዩ ጋር በሚደረግ የክፍያ ጊዜ ስምምነት ውል ውስጥ ከፍሬ ታክስና ወለድ በተጨማሪ በዚህ መመሪያ መሠረት የማይነሳው ቅጣት (በከፊል ተነስቶ ከፊሉ ሳይነሳ በሚቀርበት ሁኔታ) ብቻ ተጨምሮ ሊነሳ የሚችለው ቅጣት እንዳይካተት ሊደረግ ይችላል፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተገለጸው አግባብ ግብር ከፋዩ በስምምነቱ መሠረት ፍሬ ታክሱንና ወለዱን ከፍሎ ማጠናቀቁ ሲረጋገጥ ቅጣቱ እንዲነሳ ይደረጋል፡፡
3) በስምምነቱ መሠረት ግዴታውን ካልተወጣ ቅጣቱ በቀጣይ ባልተከፈለ የታክስ ዕዳ መጠን መሠረት የሚስተናገድ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሶስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌ

## 12. ወለድ የማይነሳ ስለመሆኑ

1) በፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ እና በሌሎች የታክስ አዋጆች መሰረት በዘገየ የታክስ እና የግብር ክፍያ ላይ የሚታሰብ ወለድ በዚህ መመሪያ መሠረት ሊነሳ ወይም ቀሪ የሚደረግ አይሆንም፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በህግ ወለድ መሰላት በሌለበት ሁኔታ በታክስ ጉዳይ ላይ በታክስ መረጃ ሥርዓቱ ወይም ሲስተም ባህሪ የተነሳ ተሰልቶ የሚገኝ ወለድ ጉዳዩ በሚመለከተው ባለሙያ መግለጫ እንዲቀርብ ተደርጎ ከሲስተም ላይ እንዲሰረዝ በቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጁ ሲወሰን ተገቢው መግለጫ ሰፍሮ ከሲስተም ላይ እንዲሰረዝ ይደረጋል፡፡

## 13. በመመሪያው የማይነሳ አስተዳደራዊ ቅጣት

የታክስ ባለስልጣኑ በሕግና በውክልና በሚሰበስባቸው የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት እና የጡረታ መዋጮ ክፍያ ግዴታን ባለመወጣት የሚጣል ቅጣት በዚህ መመሪያ መሠረት የሚነሳ ወይም ቀሪ የሚደረግ አይሆንም፡፡

## 14. ሪፖርት ስለማቅረብ

1) ቅ/ጽ/ቤቶች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ፣ 7 ፣ እና 10 ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲነሱ ውሳኔ የተሰጣቸው አስተዳደራዊ ቅጣቶች የተነሳውን የቅጣት ገንዘብ በየወሩ ተጠናቅሮና በግልጽ ተለይቶ ከወርሃዊ ሪፖርት ጋር ለፕላንና ፕሮጀክት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት መቅረብ አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተው መሰረት ቅ/ጽ/ቤቶች ሪፖርታቸውን በየወቅቱ እንዲልኩ የፕላንና ፕሮጀክት አስተዳደር ዳይሬክቶት ክትትል ያደርጋል እንደአስፈላጊነቱ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከተው ዘርፍ ሪፖርት ያደርጋል፡፡

3) የታክስ ባለስልጣኑ አስተዳደራዊ ቅጣት እንዲነሳ ውሳኔ የሰጠበትን የእያንዳንዱን መዝገብ መረጃ ከቅ/ጽ/ቤት በማጠናከር በየሩብ አመቱ ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

## 15. የተሻሩና ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች

በሥራ ላይ የነበረው መመሪያ ቁጥር 137/2010 አስተዳደራዊ ቅጣቶች ስለሚነሱበት ሁኔታ የሚገልጹ ድንጋጌዎች እና ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሰርኩላርና ልማዳዊ አሠራሮች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

## 16. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በመመሪያ ቁጥር 137/2010 መሠረት ተቀባይነት አግኝቶ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት ውስጥ ገብቶ የታክስ ዕዳውን በመክፈል ላይ የሚገኝ ግብር ከፋይ የአስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ ጉዳይ በነባሩ መመሪያ መሠረት ፍጻሜ ያገኛል፡፡

## 17. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር ተፈርሞ በሚኒስቴሩ ድህረ-ገጽ ላይ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ
ሚያዝያ 2016 ዓ.ም

አይናለም ንጉሴ
የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር